# ይህን ያውቁ ኖሯል ?

የሀገራችን የትምህርት ፓሊሲ በአራት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ሽፋን (Access ) ጥራት (Quality) ፍታሀዊነት (equity) እና ብቃት (efficiency) ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ተግባራዊ አፈፃፀሙ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ለግንዛቤ እንዲያመች ንፅፅራዊ አቀራረብን ተከትለን በ1984 ዓ.ም. በሀገሪቱ የነበረውን የትምህርት ሽፋን ደረጃና በ1999 ዓ.ም. ማለትም ከ15 ዓመታት በኋላ የታየውን ጉልህ ለውጥ እንመልከት፡፡

## ትምህርት

ሀ. የ1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት

- *1984 ዓ.ም. 8034*
- *1999 ዓ.ም. 19600*

ለ. የተማሪዎች ብዛት በ1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

*1984 ዓ.ም. 2.5 ሚሊዮን*

*1999 ዓ.ም. 14.5 ሚሊዮን*

ሐ. ዩኒቨርስቲዎች/የመንግሥት ብቻ/

- *1984 ዓ.ም. 2*
- *1999 ዓ.ም. 21*

መ. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን

*1984ዓ/ም. 20%*

*2000ዓ/ም. 97%*

ሠ. የመምህራን ብዛት 1ኛ ና 2ኛ ደረጃ

- *1984ዓ/ም. 91713*
- *1999ዓ/ም. 253542*

ረ. ከሀገሪቱ በጀት የትምህርት ድርሻ

*1984ዓ/ም. 3%*

*1999ዓ/ም. 24.6%*

| የዩኒቨርስቲዎች ሥርጭት በክልል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አዲስ አበባ | ድሬደዋ | ሶማሌ ክልል | አፋር ክልል | አማራ ክልል | ኦሮሚያ ክልል | ትግራይ ክልል | ደቡብ ክልል |
| አ.አ ዩኒቨርስቲ | ድሬድዋ ዩኒቨርስቲ | ጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ | ሰመራ ዩኒቨርሲቲ | ደሴ ዩኒቨርስቲ | ጂማ ዩኒቨርስቲ | መቀሌ ዩኒቨርስቲ | ዲላ ዩኒቨርስቲ |
| | | | | ደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ | ሃሮማያ ዩኒቨርስቲ | አክሱም ዩኒቨርስቲ | አርባምንጭ ዩኒቨርስቲ |
| | | | | ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ | መዳወላቡ ዩኒቨርስቲ | | ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ |
| | | | | ጉንደር ዩኒቨርስቲ | ወለጋ ዩኒቨርስቲ | | ወላይታ ዩኒቨርስቲ |
| | | | | ደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ | አዳማ ዩኒቨርስቲ | | ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ |

በያዝነው በ2001 ዓ.ም. የ10 ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ እየተካሄደ ሲሆን እነሱም

- በኦሮሚያ ክልል    መቱ፣ አምቦ፣እና ~~ሆለጤ~~ ቡሌ ሆራ
- በአማራ ክልል    ደብረታቦር፣ ወልዲያ
- በደቡብ ክልል    ወልቂጤ፣ ሆሳእና
- በትግራይ ክልል    አዲግራት
- በቤንሻንጉል ክልል    አሶሳ
- በአዲስ አበባ    አዲስ አበባ ናቸው።

የትምህርት መስፋፋት ለሥልጣኔና ለልማት በር ከፋች ነው። በእርግጥም ከመስፋፋቱ ጐን ለጐን የትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። የአብያተ መጻሕፍት፣ የአብያተ ሙከራ፣ የማጣቀሻ የምርምርና የስርዓት ሰነዶች የመምህራን ብስለትና የእውቀት ጥልቀት የትምህርትን መአድ በተሟላ መልኩ እንዳይዘረጋ የሚፈታተኑ ጋሬጣዎች ናቸው።

## *ታዲያስ! የእርሰዎ ሚና ምን ይሁን?*

እነኚህን ፈታኝ እክሎች ከመፍታት አኳያ የምሁሩ ትውልድ ሚና ጉልህ እንደሆነ ይታመናል። ከዚህ አንፃር እኛን የዲያስፓራው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን "እጅህ ከምን ይለናል" እኛም የሀገር ልማት በሀገር ልጅ ያምራል በሚለው ብሂል አለንልህ ልንለው ይገባል በነገራችን ላይ ሀገራችንንና ወገናችንን በትምህርት ለማልማትና እራሳችንን ጠቅመን ወገናዊ የሞራል ግዴታችንን በማበርከት የህሊና እርካታ የምናገኝበትን የባለድርሻ ሚናችንን የምንወጣበት ጊዜ አሁን ነው። አሁንም ወገናችን እጅህ ከምን ይለናልና !

*ለተሳትፎ ፣* አቶ ፈቃዱ በየነ/አማካሪ/
ስልክ ቁጥር 202 364 6388
fekadu@ethiopianembassy.org
3506 International Dr NW
Washington, DC, 20008
*ያነጋግሩ።*